ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

እሮብ ግንቦት 20 2000 ዓ.ም

**መለስ ዜናዊ ከ300 በላይ ከሚሆኑ ከግብረሰናይ ድርጅቶች ተወካዮች ጋር ስብሰባ አደረገ፡፡ ስብሰባው ብዙ ጉድ የታየበትና የተነገረበት ነበር፡፡**

እሁድ ግንቦት 17 2000 ዓ.ም መለስ ዜናዊ ከ300 በላይ ከሚሆኑ የግብረሰናይ ድርጅቶች ተወካዮች ጋር በጽ/ቤቱ አዳራሽ ስብሰባ አደረገ፡፡ የስብሰባው አለማ የግብረሰናይ ድርጅቶን አጠቃላይ እንቅስቀሴ ለማፈን ሲባል በወጣው ህግ ላይ ለመወያት ነበር፡፡ በእዚህ ስብሰባ ላይ መለስ ዜናዊ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችን በሁለት በመክፍል፣ በሰብአዊና የሲቪል መብቶች፣ በመልካም አስተዳደር፣ የህግ የበላይንትና በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ የሚሰሩትን ግብረ- ሰናይ ድርጅቶች፣ የእርዳታና የልማት ስራ ከሚሰሩ ድርጅቶች በመለየት የመጀመሪያዎቹ ምንም ስራ እንዳይሰሩ፣ በሀገር ወስጥ መንቀሳቀስ እንዳይቸሉ የሚያደርገውን ህግ ትክክለኛነት ለመግለጽ ሙከራ አድርጓል፡፡ መለስ ዜናዊ ፣ሰብአዊና ዴሞክራሲ መብቶችን በሚመለከት ትምህርትና ስልጣና የሚሰጡትን ግብረሰናይ ድርጅቶች፣ ስራቸው ወገንተኛ የሆነ የፖለቲካ ስራ ስለሆነ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ለይቶ እንደማያያቸው ተናግሯል፡፡ በእዚህም የተነሳ ከ10 በመቶ ከሚሆነው፣ ወደ ውጭ ለመጓጓዣና ስብሰባ ለመካፈያ ከሚገለገሉበት ገንዘብ ውጭ ምንም አይነት ተጨማሪ ገንዘብ ከህገር ውጭ መቀበል እንደማይችሉ ገልጧል፡፡ በእዚህ ስብሰባ ላይ ከታዩት ጉዳዮች መሃል አንዱ እንደማናቸውም ሁሉን አውቃለሁ እንደሚሉ አመባገነኖች መለስ ዜናዊ በማያውቀው የህግ ሙያ ገብቶ ከህግ አኳያ ሲያቦካ መዋሉ ነው፡፡

ይህ ግለሰብ በውጭ ሃገር እርዳታ ለሰብአዊና ለዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከራከሩ ድርጅቶን ካገር ለማጥፋት ያቀረበው ዋንኛ መከራከሪያ በፖለቲካ የዜግነትና በህግ የዜግነት መብት መሃል ያለውን ልዩነት የማያውቅ፤ ስልጣን ብቻ ስላለው ሁሉንም ነገር የሚችል የሚመስለው ግብዝ መሆኑን ያሳየበት ነው፡፡ መለስ ህግ አዋቂ ሆኖ ባቀረበው ክርክር ‹ግለሰቦች እንጂ ድርጅቶች የዜግነት መብት የላቸውም በመሆኑም በህግ መንግስቱ የተቀመጠው የዜግነት መብት ለእነሱ አይሰራም፡፡ በመሆኑም ህገ መንገስታዊ መብት የላቸውም›› የሚል ነበር፡፡ ከእዚህ ተነስቶ የወጣው ህግ ህገ-መንግስቱን የጣሰ ነው የሚል ክርክር ማንሳት አይቻልም የሚል ነው፡፡ የሚገርመው ግን ግብረ ሰናይ ድረጅቶቹ ያቀረቡት የመብት ክርክር በዜግነትና በዜግነት የፖለቲካ መብት ላይ ሳይሆን ማንኛውንም ሃገራዊ ድርጅት ህጋዊ መብት በሚሰጠው የሃገሪቱና የአለም አቀፍ ህገመንገስቶችና ስምምነቶች ላይ በመመስረት ነበር፡፡ ሀገራዊ ህጋዊ ሰውነት፣ ህገ መንግስታዊ መብትና ግዴታ በግልጽ በተደነገገበት ሃገር ግብረሰናይ ድርጅቶች ይህን ህገ-መንግሰታዊ መብታቻውን የጣሰ ስራ መንግስት ሊሰራ አይገባውም ነበር ያሉት፡፡ ህጋዊ ሰውነት ያላቸውና እንደ አንድ አካል ተወሰደው ሊከሱና ሊከሰሱ የሚችል መብት ያላቸውን ድርጅቶች ህገ መንግስቱን በሚቃረን ሌላ ህግ መብታቸውን መግፈፍ አንደማይገባ ለመግለጽ የግብረ-ሰናየይ ድርጅቶቹ ያደረጉት ሙከራ የትም አልደረሰም፡፡ በሌላ በኩል ግን የመለስ አላማ በሀገራችን ያሰፈነውን አምባገነናዊ አንድ ፓርቲ አገዛዝ በማንኛውም መንገድ ሊፈታተኑ የሚችሉ ማናቸውን ቡድኖች፣ የፖለቲካም ይሁኑ የግብረሰናይ ድርጅቶች እያነፈነፈ ለማጥፋት ከጉልበት ጀምሮ የህግን ከላላ በመጠቅም ወደ ኋላ የማይል መሆኑን በስብሰባው ላይ ታይቷል፡፡ የውጭ መንግስታት ህግን፣ ሰብአዊ መብትንና መልካም አስዳደርን በሚመለከት የሚሰጡት የገንዘብ እረዳታ በራሱ በአገዛዙ እውቅና የሰጣቸው የራሱ ተለጣፊ የሙያ ማህበራት ፤ የሴቶች የወጣቶች የብዙሃን ማህበራት ብቻ እንዲሆኑ ተደርጎ የተዘጋጀ ህግ እንደሆነ ግልጽ ሆኖ ወጥቷል፡፡ የውጭ መንግስታት የእርዳታ ድርጅቶች አንዲህ አይነቱን አይን ያወጣ የአንድን አምባገነን ፓርቲ ፍጹማዊ ቁጥጥር ለሚያጠናከር ሴራ ተባባሪ ይሆናሉ ብሎ ማሰብ ባይቻልም

በተለያዩ ሃገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ይህንን በያሉበት ለሚገኙ የመንግስት ባለስልጣናት በማስረዳት የመለስ ዜናዊ መንግስት ከእነዚህ መንግስታት ትብብር እንዳይደረግለት ዘመቻ ማድረግ እንዳለባቸው በስብሰባው ሂደትና በመለስ ዜናዊ እብሪት የተናደዱ የስብሰባው ተሳታፊዎች ጥሪ አቅርበዋል።

ከእዚህም ጋር ተያይዞ በእዚህ ስብሰባ ላይ የአንዳንድ የግብረ ሰናይ ድረጅቶች ተወካዮች ያሳዩት አድርባይነት፣ህሊና ያለዉን ሰው የሚያሸማቅቅ ነበር። ከመለስ ዜናዊ ጋር በአካል ለመተያያት እድል ስላገኙ ፈጣሪያቸውን የሚያመሰግኑ መሆናቸውን፣ የመለስ ዜናዊን ብልህ አመራር ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውና ግብረሰናይ ድርጅቶች በውጭ እጅ ይመራሉ፣ አጥፍተዋል ብለው  ጠቅላይ ሚ/ሩ ካሰቡ በእርስዎ አመራር እንስተካከላን የሚል ንግግራቸው መብትን ለማስከበር ሳይሆን ለማደግደግና ጫማ ለመሳም በእዚህም የተነሳ በሌላዉ የመብት ኪሳራ የግል ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በስብሰባው መገኘታቸውን የሚገልጽ፣ ብዙሃኑን ያሳፈረና ያዋረደ ድርጊት እንደሆነ አንዳንዶቹ ተሰብሳቢዎች በቁጭት ሲገልጹ ተደምጠዋል። ከሁሉ አሳፈሪ የነበረው መለስን የመሰለ አምባገነንና ነፍሰ ገዳይ ሲያወድሱ የታዩት ክብር-የለሽ ግለሰቦች ሳይሆኑ ቀደም ብሎ በተመሰሳይ ጉዳይ ላይ ከፍትህ ሚንስትሩ ጋር  ውይይት በተደረገበት ወቅት ደ/ር ሚናስ ህሩይ ያቀረበውን ለምን የአብአዊና የዴመክራሲ መብት ተከራሪ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች አግዳችሁ ለእኛ የልማት ስራ ለምንሰራው ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች በነጻ የመንቀሳቀስ መብት አትሰጡም የሚለውን አሳፈሪ ሃሰብ ደጋግመው ያነሱ ተወካዮች በእዚህ ስብሰባ መታየታቸው ነው። ለግበረ ሰናይ ድርጅቶች  ‹የድህነት ጌቶች› የሚል መጥፎ መጠሪያ ያተረፉላቸው አንዲህ አይነቶቹ ስግብግብ ግለሰቦች መሆናቸው ጥርጥር የለውም።